

# የማለዳ ድባብ

በዕውቀቱ ሥዩም

አዳዲስ ግጥሞች

# የማለዳ ድባብ

(የአዳዲስ ግጥሞች መድብል)

በዕውቀቱ ሥዩም

2009 ዓ.ም

© በዕውቀቱ ሥዩም 2009 ዓ. ም
የደራሲው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው።

በመጀመሪያ ሐምሌ ፳፻፱ ታተመ።

Copyright © Bewketu Seyoum 2017
All rights reserved, including the right to reproduce this book thereof in any form whatsoever.

የሽፋን ሥዕል - "Procession from the Court of St. Michael at Ankobar" (1842) in Scenes of Abyssinia by Johannes Martin Bernatz

**የደራሲው ሌሎች ሥራዎች**

| | | |
|---|---|---|
| ከአሜን ባሻገር | (ታሪካዊ ወግ) | – 2008 ዓ. ም |
| መግባትና መውጣት | (ልብወለድ) | – 2002 ዓ. ም |
| ስብስብ ግጥሞች | (ግጥም) | – 2001 ዓ. ም |
| የ'ማት ዳር ሀሳቦች | (ግጥም) | – 2000 ዓ. ም |
| እንቅልፍ እና እድሜ | (ልብወለድ) | – 1999 ዓ. ም |
| በራሪ ቅጠሎች | (ልብወለድ) | – 1996 ዓ. ም |
| ኗሪ አልባ ጎጆዎች | (ግጥም) | – 1995 ዓ. ም |



ጎሕ ገስግሶ
ደርሶ
ጽልመት ቢያባርርም
የማለዳ ድባብ፥ ህብሩ ገጹ ቢያምርም
ሰው ፀሐይን አምኖ፥ ፋኖሱን አይሰብርም።

## ግጥምና የዘመን መንፈስ

ኢትዮጵያ የአንባቢና የጣፊ ሳትሆን የተናጋሪና የአድማጭ አገር ናት። የጽሕፈት ታሪክ እንደነበረን አልዘነጋሁም። ግን የጽሕፈት ሥራ ለብዙ ዘመን ከጥቂት ምድራዊና ሰማያዊ ባለሥልጣኖች ፍጆታ ተርፎ ለሰፊው ባላገር የሚዳረስ አልነበረም። ሰፊው ገባር ሕዝብ ይናገራል እንጂ አይጽፍም። ያዳምጣል እንጂ አያነብም። ሮሮውን እና ደስታውን፣ ምርቃቱንና ርግማኑን በአጭር ስንኝ ሲገልጥ ኖሯል።

ለንኞች አጭር ያደረጋቸው የትውስታ ሕግ ይመስለኛል። አጫጭር ግጥሞች ከገጣሚው ምናብ ለመፍለቅ ይፈጥናሉ። እንዲሁም በቃል ለማጥናት ይቀላሉ። ረጃጅም ግጥሞች የተለመዱት ያስያዙትን የማይለቀው ብራና ሲለመድ ይመስለኛል።

ሲፈርድባት፣ ኢትዮጵያ ለአያሌ ዘመናት የጦር ሜዳ ሆና ቆይታለች። ጦርነት ባንድ ገጹ ሰይጣን በሌላ ገጹ ፈጣሪ ነው። ፈጣሪ ያልኩትን አሰቲ በሥነግጥም በኩል ላብራራው። ጦርነት ዋዜማ ላይ የንጉሥ አዋጅ ይደመጣል። አዋጅ ስናስብ "ምታ ነጋሪት ከተት ሰራዊት" የሚል ስንኝ ትዝ ይለናል። "አመልህን በጉያህ ስንቅህን በአህያህ" የሚለው ያዋጅ ማስርያም ይታወሰናል። በጦርነት መባቻ ላይ ወገን በስንኝ ራሱን ያወድሳል፤ ጠላቱን ይወቅሳል። ይህንን ፉከራ ብለን እንጠራዋለን።

ከድል በኋላ በሕይወት የመትረፍ እድል ያገኙት ገድላቸውን በስንኝ ይተርካሉ። ጦር ባለበት ሞት ይኖራል። የድሮ ሰዎች ሙታንን ሲቀብሩ አለለቃሽ የሚባል ሰው አስከትለው ወደ መካነ መቃብሩ ይሄዳሉ። አስለቃሾች ከሰው ሕይወት ጋር የተያያዙ አጫጭር ግን ጥልቅ ሀሳብ ያላቸውን

ጀግናና ብርሌ፥ ቶሎ ይሰበራል
ፈሪ ተራራ ነው፥ ዘለዓለም ይኖራል።

የሚለው ይገኝበታል።

ሀሳቡን ተቀበልነውም አልተቀበልነውም ገጣሚው ከተለምዶው አመለካከት ፈንገጥ ብሎ ለማሰብ መድፈሩን ልናደንቅለት እንገደዳለን።

ከሀሳቡ ባሻገር ግጥሙ በቅርጽ ረገድ የምርጥ ግጥም ማሳያ ሊሆን የሚችል ነው። ገጣሚው ያዘቢት ገጣሚ ቢሆን ኑሮ፤

ጀግና ሲንቀዠቀዥ፥ ቶሎ ይለየፋል
ፈሪ ግን ረጅም እድሜ ያሳልፋል።

ብሎ ገጥሞ ይገላገል ነበር።

አንድን አሪፍ ገጣሚ አሪፍ የሚያደርገው ትልቅ ሀሳብ ማንሳቱ አይደለም። ሀሳቡን አሳምሮ የሚገልጥለትን ምስል ከቃሎች ሁሉ መርጦ መጠቀሙ ነው።

የከቱ ገጣሚ ጀግንነት እና ፈሪነት የተባሉትን ረቂቅ ሀሳቦች ብርሌ እና ተራራ በተባሉ ግዙፍና ገላጭ ምስሎች ለውጦ ማሳየቱ ተዋጥቶለታል።

በዘመናችን የግጥም መድብሎች የመውጣታቸውን ያክል ጥራት የላቸውም የሚል ሂስ ከየአቅጣጫው ይደመጣል። ይህን ሂስ በደፈናው ውድቅ ማድረግ አይቻልም። ምናልባት ይህንን ከዘመኑ መንፈስ ጋር እያይዞ መፈተሽ ይቻል እንደሆን ግን ልሞክር።



የኔ ዘመን ቃናው የጠፋበት ቅኝቱ የተበላሸበት ዘመን ነው። አንድ ሰው ካዲስ አበባ ጎዳናዎች ባንዱ በእግሩ ሲንሸራሸር በዙርያው የሚያየው ምንድነው? ... የፈረሰ የድሮ ቤት፤ የተቦዳደሰ አውራ ጎዳና፤ የእግረኛ መንገድ ዘግቶ የተገተረ የሰሚንቶ ተራራ፤ በዘፈቀደ የተደረደረ መስታወት ለበስ የፎቅ ሰንሰለት ወዘተ ...

አዲለ አበባ ከከተማነት ወደ ግዙፍ ምስቅልቅልነት ተለውጣለች። ከአካባቢያችን ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያለን ፍጡራን እንደመሆናችን መጠን በዙርያችን ያለው ምስቅልቅል በባህርያችን፣ ባስተሳሰባችን፣ በቋንቋችን እና በግጥሞቻችን ላይ የራሱ ጫና አለው።

ገጽታው በተረበሸ፣ እንደ ዝግመተ ለውጥ በድንብር በሚመራ አገር ውለጥ እየኖሩ በለከነ ቋንቋ፣ ወግ ያለው ሥነጽሑፍ የሚያቀርቡ ደራሲዎች ካሉ ከዘመናቸው የመነኑ መሆን አለባቸው።

በመጨረሻም ግጥሞቼ የተሰበሰቡበትን ሁናቴ ልናገር። "ኗሪ አልባ ጎጆዎች" የሚለው የግጥም መድብሌን መሠረት የሆኑት ጋዜጦች ላይ እልካቸው የነበሩት ግጥሞች ናቸው። ዛሬ የጋዜጣ ወረት አልቆ የኢንተርኔት መድረክ ተከፍቷል። እኔም በማህበራዊ ሚድያ ላይ ካስነበብኳቸው ግጥሞች ማህል መርጬ፣ ማስታወሻየ ላይ ካሳደርኳቸው ግጥሞች ጋር ብደምራቸው ላንድ መድብል የሚበቁ ሆነው አገኘኋቸው። እንሆ ...

በዕውቀቱ ሥዩም
ሰኔ 2009 ዓ.ም
አዲስ አበባ

## ምስጋና

ይቺን መድብል፥ እንደምትሆን እንደምትሆን ያደረጉልኝን ወዳጆቼን ሕይወት ማሩን እና ብሩክ አብዱን አጥብቄ አመሰግናለሁ።




ግጥምና የዘመን መንፈስ V

ሐውልቴ ገናና 17
እውነት እንደሎሌ 18
መአዛሽ ፈወሰኝ 20
ሙሾ ላመለጠ ወጣትነት 21
ልረሳሽ እየጣርኩ ነው 22
ላባቴ 23
እኛ 24
ደስታ ቢራቢሮ 25
ከልጅነት ፍቅር አንዲት ጠብታ 26
የተካደ ትውልድ 28
እኔ ወድሻለሁ 29
ታዲያስ ምን አዲስ ነገር አለ? 30
በዝግ በር 32
እመ መከራ 33
የቴዎድሮስ ማመንታት በመቅደላ 34
ህልሜን አደራ 36
መትረፌ ገረመኝ 37
ገንዳው 38
አንሶላየ ውስጥ ልሙት 40
ከተለየሁሽ ወድያ 41
ተሰፋ እንደ ምትሐት 42
በቃኝ 43
በሞቷ ፊትለፊት 44
የመኖር ትርጉሙ 45
አስታራቂ የሰም 46
ላንድ መስቲካ ሻጭ ብላቴና 47
ግን አንድ ሰው አለ 48

በምናልባት ኑሮ 49
ያንድ ምሽት ናፍቆት 50
የምድረበዳ በረከት 51
ላጣሽ አቅም እጣሁ 52
ጠብ እና ጥበብ 53
አለሽ ወይ 54
በረከተ መርገም ፪ 56
ኢትዮጵያዊ ነኝ 58
ሱ !! 59
እንጉርጉሮየ 60
አስቢኝ 61
ኬላ ነኝ 62
ትዝታን ባንበር 63
እንደምነሽ ሸገር 64
ወይ ገራምነቴ 66
መኖር ወይስ አለመኖር 68
ታሪክ የሆነ ሌሊት 69
እንባየን የት ላርገው 72
አገር እንቁጣጣሽ 73
ምኞት እሽሩሩ 74
አባ ይፍቱኝ 75
ማንባት ነው ያሰኘኝ 76
ጥቂት ነው ምኞቴ 78
ካንቺ ጋራ 79
ራሴን በራሴ 80
ላንዲት ተመጽዋች ብላቴና 81
ይድረስ 82
ሰቆቃወ በውቄ 84
ሙግት 86



ከዚህ ወድያ አልወድሽም 87
ማንም ግድ አይሰጠው 88
ሙሾ ለከሰሙች ተፈጥሮ 90

ጉደኛ ስንኞች 93

ሙሾ እና ባለቅኔ 97

## ሐውልቴ ገናና

እኔን የሚዘከር፥ ሐውልት ለምትቀርጹ፥
ገጼን ለምትስሉ
ሕይወቴ ሲጨመቅ፥ ይሄ ነው ምስሉ
የተረፈረፉ፥ የቢራ ጠርሙሶች
ንዋያተ-ቡሶች
ታፔ ላይ ተነሥተው፥ የሚያርጉ ጭሶች
በወጥ የተኳሉ
ሰፋፊ ዳታኖች
ባመድ የተሞሉ
ገጣባ ሰሀኖች፤

አሜን! አሜን ይሁን! ሐውልቴ ገናና
ቀመር ባልፈለሰፍ፥ አገር ባላቀና
ኖሮ ማለፍ ብቻ፥ ጀግንነት ነውና።

## እውነት እንደሎሌ

ከለታት ባንዱ ለት፥ ደም በደመነበት፥ በነውጠኛው ጊዜ
የጎጃሙ መስፍን፥ ራስ አዳልና የላስታው ጎበዜ
ገብር አልገብርም፥ ይዋጣልን ብለው
ለመግደል ለመሰለብ፥ እጅግ የቋመጠ፥ ሰራዊት መልምለው
ጠመንጃ ወልውለው፥ ሰይፋቸውን ስለው፥
ጨሬውን እሹለው
ዛቻ ተለዋውጠው፥ ለመተናነቂያ፥ የማይቀር ቀን ቆርጠው
ለፍልሚያ ለግልቢያ፥ የተመቸ ስፍራ፥ ድልድል ሜዳ
መርጠው፤

በተፋጠጡበት፥ በውጊያ ዋዜማ
አንድ ብልጥ ደብተራ፥ ዜናውን የሰማ
እንደ ባህታዊ ፥ ወይባ ዳባ ለብሶ
የላስታው ጎበዜ፥ ወደ ሰፈረበት፥ ጋለበና ደርሶ
"የርስዎ ሰራዊት፥ ባዳል ጭፍራዎች ላይ፥ እንደሚበረታ
በልሜ አሳይቶኛል፥ ያባቶችዎ አምላክ፥ ትናንትና ማታ"
ብሎ ተናገረ
ተናግሮም አልቀረ፤

ወደዚያኛው ጎራ፥ ገሰግሶ ሄደና
"ጌታው ራስ አዳል፥ ድል አድራጊው ጀግና
ህልሜ ወሰል እርጎ፥ እንደገለጠልኝ፥ የነገው ድል ነሸ
ርስዎ ኖትና
እኔን ነቢይ እርጎ፥ ለላከልሁ አምላክ፥ ያቅርቡ ምስጋና!"

ይህንን የሰማ፥ ጓደኛው ቢደንቀው
እንዲህ ሲል ጠየቀው
"ነገር እንደማብረድ፥ ሰላም እንደማውረድ፥ እንደመገላገል
ምን ይሉት ፈሊጥ ነው፥ አሳትና ጭድን፥ በተራ መሸንገል?



ቢቃልህ ተማምኖ፥ ታግሎ የተረታ
የት ትገባ ይሆን፥ እንደዘበትክበት፥ የባነነ ለታ?"

ይህንን ወቀሳ፥ አድምጦ ደብተራው
ቃሉን አስማምሮ፥ መለሰ በተራው፤

"በወትሮ ልማዱ፥ ሰው መተራረዱ፥ ፈጽሞ ባይቀርም
አንዱ ተሸንፎ፥ አንዱ እንደሚያሸንፍ፥ እያጠራጥርም
ያሸነፈው መስፍን፥ በትንቢቴ ታምኖ፥ ደስ ብሎት ሲሾመኝ
የተሸነፈው ግን፥ ያልሁትን አስቦ፥ እኔን መቅጣት ቢመኝ
ከምኞት ባለፈ፥ ከቶ ምን ያመጣል
የተሸነፈ ሰው፥ ስልጣኑን ያጣ ቀን፥ ሁሉን ነገር ያጣል፤

በዚች የጉድ ምድር፥ መሸነፍ ነው ወንጀል፥
ይህንን አውቃለሁ
የተረታ ድኩም፥ ራሱን ሊያጥናና፥
'እውነት ያሸንፋል' ሲለኝ እስቃለሁ
ይልቅ አሸናፊው፥ እውነትን ያበጃል፥ ባምሳሉ ጠፍጥፎ
ሲሻው ያወርሳታል፥ ለቀጣዩ ትውልድ፥ በጽላት ላይ ጥፎ፤

ምድር ገበያ ናት፥ አንዱ ያንዱ ሸቀጥ፥ አንዱ ያንዱ እሞሌ
ሐቅም የላት አቅም፥ ሆና ትኖራለች፥ ያሸናፊው ሎሌ
ያዳም ልጆች ልብም፥ ጠንሳሽ የሚጠብቅ፥
የጠብ ድፍድፍ በርሚል
ግልብ ሰው ብቻ ነው፥ ሰላምን በሰብከት፥
እሰፍናለሁ የሚል
አጉል ከምትለፋ፥ በዚች የጠብ ዓለም፥ ጠብን ልታስወግድ
ቂሎች ሲፋለሙ፥ በደማቸው አትርፍ፥ ባጥንታቸው ነግድ።"

## መአዛሽ ፈወሰኝ

ጎራዳ አፍንጫየን
ጎራዴ እፍንጫየን
ከሰገባው ሰቤ
ስምግሽ ቀርቤ
አንገትሽ ሽነት ዛፍ
ጡትሽ ደብረ-ከርቤ

እፎይ!!!

እንዲያው ሲፈርድብኝ፥ ቤቴ አዲስ እበባ
ሰማዩ ጥንብ ነው፥ መሬቱም አዛባ
ዓይን ጆሮ ምላስ፥ ለኑሮ ሳያንሰኝ
ምን በድየው ጌታ፥ አፍንጫ ሰገሰኝ
እያልሁኝ ሳማርር፥ አንቺን ልኮ ካሰኝ
መዳኒት ሆነና፥ መእዛሽ ፈወሰኝ።



## ሙሾ ላመለጠ ወጣትነት

ሳይደምን ይዘንባል
ይዶፋል
ከደጃፌ ግርጌ፥ የሕይወት ጎርፍ ያልፋል፤

የከንፌ ርጋፊ
አንድ የላባ ነዶ
ያካሌ ቅራፊ
የቀረ ተጎርዶ
ተጠርጎ ሲወሰድ፥ በጥሞና ኢያየሁ
ይሄው ቁጭ ብያለሁ፤

ሲጋልብ በፊቴ፥ ይህ የውሀ ሰጋር
ጀምበሬን አየኋት
ተጠርጋ ስትሄድ፥ ከሰርዲን ጣሳ ጋር

የልጅነት ቅርሴ
ድዴ ያባረራት፥ ያች የወተት ጥርሴ
ካሮጌ ቆርኪ ጋር፥ አብራ ተቀላቅላ
ባረፋ ተከባ፥ በጎርፍ ጀርባ ታዝላ
ስትሄድ እያየሁ
ይሄው ቁጭ ብያለሁ፤

የመጀመርያዋ፥ የጉንጨ ላይ ቡግር
የመጨረሻዋ፥ የራሴ ላይ ጠጉር
ከሳር ከትቢያው ጋር፥ እንደተቃቀፉ
በጎርፉ ጀርባ ላይ፥ እየተንሳፈፉ
እንደዋዛ ሲያልፉ
በጥሞና እያየሁ
ይሄው ቁጭ ብያለሁ።

## ልረሳሽ እየጣርኩ ነው

በጣራው ላይ ሲረማመድ፥ የዝናቡ ልዝብ ኮቴ
መጋረጃው ሲውለበለብ፥ ሰንደቅ ሆኖ ለመስኮቴ
ዋርካው በቅጠል ጽዋ
ውሀ ሲያቁር ከሕዋ
የምድርን ጉሮሮ ሲያርስ
መሬት ፍጥረትን ስትጸንስ
በዚህ ሁሉ ጸጋ ማህል፥ ያንችን መሄድ ስተምነው
ኢምንት ነው ምንም ነው
ልረሳሽ እየጣርኩ ነው፤

መጣ መጣ መጣ፥ የዝናቡ ኮቴ እየለ
ከረምት የፍጥረት መሲሕ፥ በቀጠሮው ከተፍ አለ
ስሱ የጉም አይነርግብ፥ ውብ ገጽሽን ሸፋፈነው
የርጥብ አፈር ርጥብ ሽታ፥ ውብ ሽቶሽን አዳፈነው
ልረሳሽ እየጣርኩ ነው፤

የዝናቡ ኮቴ ይደምቃል
እንደብሰል ሾላ ፍሬ፥ አሮጌው ሰማይ ይወድቃል
እንኳን የእግርሽ ኮቴ፥ ጎዳናሽም ታጥቦ ያልቃል፤

ልረሳሽ እየጣርኩ ነው ...



## ላባቴ

ሰው ብቻ አይደለህም፥ ካፈር ወጥተህ ላፈር
መላክ ነህ፥ ሉሲፈር*
ክብርህ ማንነትህ፥ ባመጽ የሚታፈር
የማትንበረከክ
የማትርመጠመጥ
ከባለጌ ዙፋን፥ በርጩማ የምትመርጥ፤

ያለ ባሕር ሰርጓጅ፥ ያለ ሙሴ በትር
በመታገስ ብቻ፥ ባሕር የምትመትር
ካዘልከኝ ጀምሮ፥ እንኮኮ ጫንቃህ ላይ
ከፍታውን እንጅ፥ ዝቅታውን ሳላይ
እንደንስር መጠቅሁ፥ እንደ ምሥራቅ በራሁ
የገዛ ክንፎቼን፥ እንደ ዳንቴል ሠራሁ፤

በርግጥ ድሀ ነበርክ
ከሰላምታ በቀር፥ የማታበረክት
ነጠላህ መናኛ፥ ሰውነትህ የክት፤

በርግጥ ድሀ ነበርክ፥ የነጣህ የጠራህ
ከጦር ሜዳ ይልቅ፥ ገበያ ሚያስፈራህ
ቤሳ ባታወርሰኝ፥ አወረስከኝ ትግል
የትም እንዳይጥሰኝ፥ ሕይወት እንደ ፈንግል፤

እባየ ብርሃን
እባ የምሥራቅ በር
ገመና ሸሻጊ፥ እንደ ካባ ገበር
እባቴ ባትሆን፥ ምን ይውጠኝ ነበር።

*(* 'ሉሲፈር' አጥቢያ ኮከብም ማለት ነው)*

## እኛ

እኛ
ኖረን እኮ እናውቅም
ከባሕር ጠርዝ ላይ
እንደከቡር ድንጋይ፥ እሬሳ ስንለቅም፤

ከሙሴ ተምረን
ባሕር መግመስ ሲያምረን
በባሕር ተገምሰን
በታንኳ ሄድንና፥ በሳጥን ተመለስን፤

እኛ
የካሌብ ወራሾች፥ ያሉላ 'ባ ነጋ
የምኒሊክ ልጆች፥ የና'ብዲሳ አጋ
እንደሚጨጭት መንጋ
በጭልፊት ዋርካ ሥር፥ እንደተበተነ
አቅማችን ጋሻችን፥ ጩኸት ብቻ ሆነ፤

በቅል ማሕፀን ውስጥ፥ ባጉል ቀን ተፈጥሮ
እንደሚኖር ተባይ፥ ታፍኖ ታጉሮ
ማን ነው የሚነብን፥ መውጫ የለሽ ኑሮ።

*(በስደት ወጥተው የባሕር እራት ለሚሆኑ
ኢትዮጵያውያን እና ኤርትራውያን ወገኖቼ)*



## ደስታ ቢራቢሮ

ደስታ ቢራቢሮ
እኔ ጀብደኛ እዳኝ
ስትከንፊ ስከተል፥ የእድሜ መንገድ ከዳኝ

ሳሎኔ ዱር ሆኖ
በግንድ በቅርንጫፍ፥ በሣር ተሸፍኖ
ከኮርኒሴ በታች፥ ወፍራም ጭጋግ ሰፍኖ
እኔም እድሜ ልኬን፥ የማያድግ ሕፃን

እድገቱ
ቁመቱ
ባስማት የተገታ
ነጋ ጠባ ዝላይ፥ ሁለዜ ጨዋታ
በሄደበት ለማጅ
ነፍስን በወንፊት፥ ውሀን በጨርቅ አጥማጅ፤

ዓመት ታመት ጮርቃ
ለሹመት ማይታጭ፥ ለዋለ የማይበቃ፥
ሆኘ ቀረሁ በቃ?

ደስታ ቢራቢሮ
በጣቶቸ ማህል፥ ቀለምሽ ተነነ
ተከትየሽ ስከንፍ፥ ላባየ በነነ
ክንፌ ተመለጠ
ጥላሽን ሳሳድድ፥ ዘመኔ አመለጠ።

## ከልጅነት ፍቅር አንዷት ጠብታ

በሰላሳው መንገድ
የትየለሌ አግር፥ እንደሊጥ ባቦካው
ጸአዳ ጣትሽን፥ ጉድፍ እንዳይነካው
ማጡን እየዘለልሽ፥ ዳጥ ዳጡን እያለፍሽ
ጤዛ የወረረው፥ ዛፍ እየተደገፍሽ
ትንሽ ስትመጭ፥ ብዙ ስታዘግሚ
ሁለቴ ተራምደሽ፥ አስሬ ስትቆሚ
ስተደናገረው፥ መንገድ ስትጠቁሚ
የተላከ ሕፃን፥ አሰቁመሽ ስትስሚ፤

እኔ ሰናፍቅሽ
እኔ ሰጠብቅሽ
እንደጉድ ተውቤ
ላማልልሽ ጥሬ
በጀንትራ ዘይቤ
ጠጉሬን አበጥሬ
ጅማት እያጠበቅሁ፥ ጅማት እያላላሁ
የገዛ ከንፈሬን፥ ቀርጥፌ እየበላሁ
ሰጠብቅሽ በጣም
ምስልሽ ነው እንጂ፥ አካልሽ አልመጣም፤

ባይኖቼ ሰፈልግ
መሰኮት እከፍትና
ሌላ ነው የሚያልፈው፥ በሰፊው ጎዳና
ያው ገጣባ አህያ፥ ያቻት ድኩም በቅሎ
በግ እየጎተተ፥ አለፈ ቆሰኛ
ቅርጫት ያጎበጣት፥ ሚስቱን አስከትሎ
ያውና ድሀ እደግ፥ መንገድ ዳር የተኛ



የተጎነጎነ፥ የሣር አምባር መስሎ፤

ባይኖቼ ሳማትር፥ መስኮት እከፍትና
ሌላ ነው የሚያልፈው፥ በሰፊው ጎዳና፤

ሁሉም ተሰውጦ
ያ ገጣባ አህያ፥ ጸጉር አቆጥቁጦ
ያች ድኩም በቅሎ፥ ሲጋር ፈረስ ቀድማ
ቆለኛው ሰውየ፥ ሙከት በጉን ሸጦ
ለሚስቱ ነጭ ሻሽ፥ ለሱ ሸራ ጫማ
በትርፉ ሸምቶ
ሁሉም ከሄደበት፥ ቀንቶት ተመልሶ
ሁሉም ከድቀቱ፥ በወግ ተፈውሶ፤

እኔ ብቻ ቀረሁ
መንገድሽ ረዝሞ፥ ባሳብ እያሳጠርሁ
አንቺን እየናፈቅሁ
አንቺን እየጠበቅሁ
ጅማት እያላላሁ፥ ጅማት እያጠበቅሁ።

## የተካደ ትውልድ

የተካደ ትውልድ
አይዞህ ባይ የሌለው
ታዳጊ የሌሰው
ወይ ጠባቂ መላከ፥ ወይ እበጀ በለው
ደርሶ ከቀንበሩ የማይገላግለው፤

የተካደ ትውልድ

አብዝቶ የጾመ፥ ተግቶ የጸለየ
ጥቂት መና ሳይሆን፥ ጥይት ሲዘንብ ያየ
እድሜ ይፍታህ ተብሎ፥ የተወለደ ለት
እምባሩ ካቴና፥ ማተቡ ሰንሰለት
ምቾትን የማያውቅ፥ ረፍት የተቀማ
እልጋው ያጋም እሾህ፥ መኝታው የሳማ፤

የተካደ ትውልድ
ሞቶ እንኳን ሬሳው፥ አይላላለት ቀንበር
በዘብ እጅ ተገድሎ፥ በሹም የሚቀበር
ከጡት እስጥል በላይ፥ ኑሮ የመረረው
እንዳይሄድ ጎዳናው፥ የተደናገረው
ድል ያልሰመረለት፥ ትግል ሳይቸግረው፤

የተካደ ትውልድ፥ በሥጋ በነፍሱ
በቀልቡ በገላው
ኧረ ምንድን ይሆን?
ምንድን ይሆን መላው?



## እኔ ወድሻለሁ

እኔ ወድሻለሁ
ታስሮ እንደመፈታት
እንደጣእስ ውበት
እንደዝሆን ብርታት
ዳዊትን ከጎልያድ
ደርቦ እንደመምታት፤

እኔ ወድሻለሁ
ጠም ውሎ እንደመጉረስ
ወልዶ እንደመታረስ
ቆምቦላ እንደመድረስ
ካላሙዲ ንብረት
ግማሽ እንደመውረስ፤

እኔ ወድሻለሁ
እንደመቅደስ እጣን
እንዳፍለኛ ስልጣን
እኔ ያንች ቡዳ
ያንች ልዝብ ሰይጣን።

*(አዝማቹ የገብረ ክርስቶስ ደስታ ነው)*

## ታዲያስ ምን አዲስ ነገር አለ?

ታዲያስ ምን አዲስ ነገር አለ?

ጀንበር በምራብ ወጣች
ሮብ ሰኞን ተከተለ
አጋዴን ላይ በረድ ፈላ
ሰሃራ ላይ ዝናብ ጣለ?

ታዲያስ ምን እዲስ ነገር አለ?

ኑሮ ታምና ተሻለ
ሸከሙ ከትናንት ቀለለ
አገር ጣጣውን ፈታ፥ ወይስ ጣጣውን አከለ
ዜጋው ራሱን ቻለ፥ ወይስ ራሱን ደለለ
"የጌታ ፈቃድ ይሁን ብለን ዝም አልን" እያለ?

ታዲያስ ምን አዲስ ነገር አለ?

ማን ነበሩ እትየ አንትና
መቸም የድህ ስሙ፥ ለትውስታ አይበቃምና
ምነው እኒያ አንኳ
በቁጥር ለማይሰፈር አመት
የሚጎበኝ እንጂ የማይሸመት
የቲማቲም ጉልት ዘርግተው
እንደብቅል ቀኑን ሙሉ፥ ከጸሐይ ሥር የሚሰጡ
ሙያቸውን ለወጡ
በሙያቸው ተለወጡ
ከችግራቸው ወጡ
ወይስ በችግራቸው ተዋጡ
ከብረው መኪና ገዙ፥ ወይስ በመኪና ተዳጡ?



ታዲያስ ምን አዲስ ነገር አለ?

ያዲሳባ ሀብታም እናኗኑን ከለሰ
ጋራ ቦርጩን በዲናሚት አፈረሰ
ለፉንጋ ሴት ገንዘብ ለገሰ
ከብረት አንቀልባ ወርዶ በግሩ ተንቀሳቀሰ?

ድሀውሳ እንዴት ሆነ?
ፍላጎቱ ረገበ
ጥሬ ሥጋ ጠገበ
በፋሲካ ለለውጥ ያከል ሰላጣ ተመገበ?

ታዲያስ ምን አዲስ ነገር አለ?

## በዝግ በር

እንደድሮ ቀሚስ፥ መሬት እየጠረግሁ
የእግርሽን አሻራ፥ ተግቼ እየፈለግሁ
እንደጉም
ሳዘግም
እንደሠርዶ ለሳብ
ባካል ብታመልጭኝ፥ ደረስኩብሽ ባሳብ፤

ልብ አይገታም በሩ፥ ልብ አይገታም መስኮት
በዝግ ቤትሽ ገባሁ፥ ልክ እንደ መቆኮት።



## እመ መከራ

ኢትዮጵያ እመ መከራ
የግዜር መመራመሪያው
የስቃይ ቤተ-ሙከራ
መውደቅማ ነበር ያባት
እንደ ያሬድ እስከ ሰባት
እንደ በላ ብላቴና
የእንከርዳድ ሙልሙል እንጎቻ
የትውልዱ እጣ ፋንታ
መውድቅ፥ መውድቅ፥ መውድቅ ብቻ!

## የቴዎድሮስ ማመንታት በመቅደላ

እቴ የተመኙ፥ ውዴ ውዴ ውዴ
ከጉድጓዴ አጠገብ፥ የበቀልሽ አበባ
የመሞት ምክንያት፥ ብዙ ቢኖረኝም
የመኖር ምክንያት፥ አንችን ብቻ አግኝቸ
ሞት እሾህ ገላውን፥ ለማቀፍ ቢያምረኝም
ጥቂት እመንትቸ
ጣፋጭ ገሃነሟን፥ ጭኗን ለማን ትቸ
መንገድ የሚያሳየኝ፥ ዓይኗን ለማን ትቸ
ወይን ፈገግታዋን፥ ሳቋን ለማን ትቸ፥
እያልሁ እመንትቸ፤

እቴ የተመኙ
ለካ እንደዚህ ያምራል፥ የምሥራቅ ወገግታ
ለካ እንደዚህ ውብ ነው፥ የሰማይ ፈገግታ
ለካ ልብ ይሰርቃል፥ የዛፎች ኮሽታ
ለካ አጣን ያሰንቃል፥ የርጥብ አፈር ሽታ
ደጁ ላይ እስኪደርስ፥ የሞት ኮቴ ዳና
ሰው የኑሮን ዋጋ፥ መቸ ይረዳና፤

ላጭር ስልጣን ዘመን፥ ላንዳፍታ ክራሞት
ባቅመቢስ ሕዝብ ላይ፥ የነዛሁት ሺ ሞት
ሲያንዣብብ በኔው ላይ፥ በኮሶ ላይ እሞት
ደብልቄ እንደጠጣሁ
ጫፍ እልባ ምሬቱን
መግለጫ ቃል እጣሁ፤

እቴ የተመኙ
ሸሸግ እመቤቴ
እጅግ የወደድሽኝ፥ ያውም ከነብደቴ
ያለፈው ትዝታ፥ ባይን ጠርዝ ሽው ሲል



እንደ ቆንጆ ልጅ ኩል
ምንም ጀግና ቢሆን፥ ሰው ለሞት አይቸኩል።

*(እቴ የተመኙ የአፄ ቴዎድሮስ ተወዳጅ ፍቅረኛ ነበረች። አፄ ቴዎድሮስ በመቅደላ አምባ ላይ ከማይጋፋው ጠላቱ ጋር በተፋጠጠበት በዚያ ቀውጢ ወቅት የናፍቆት ደብዳቤዎች ይልኩላት ነበር። ባንዱም ደብዳቤ ውስጥ* ***"አይዞሽ በእግዚአብሔር ኀይል አፈር ካለበስሁ ሳላይሽ አልቀርም። አትባቢ"*** *የሚል በተስፋ መቁረጥና በተስፋ ማድረግ ማህል የወደቀ ቃል ይነበባል ... የኔን ግጥም የቀሰቀሰው ይህ አንጀት የሚበላ መስመር ነው።)*

## ህልሜን አደራ

ባይመረመሬ፥ ጥበብ ተሸቀርቅሮ
ከወርቃማ ብርሃን፥ ከብርማ ጸዳል
የተሠራ ሸማ፥ ማግኘት ብችል ኖሮ
ከውብ እግሮችሽ ሥር፥ እዘረጋው ነበር
ግና ምንም የለኝ፥ ከህልሞቼ በቀር!

የኔ ውድ እንግዲህ
ህልሜን እግሮችሽ ሥር፥ ከዘረጋሁ ወዲህ
ዝግ ብለሽ እርገጪ፥ ዝግ ብለሽ ሂጂ
ህልሜ ላይ ነውና፥ የምትራመጂ።

*(ከዊሊያም የትስ "The Cloths of Heaven" የተመለሰ)*



## መትረፌ ገረመኝ

እንዳገው ጃንጥላ፥ ሰማይ ተሸከርክሮ
እንዳይናፋር ፈረስ፥ መሬቱ ደንብሮ
የተደገፍኩበት፥ ከዘራው ተሰብሮ
ሁሉ ሲያዳልጠኝ
ሁሉ ሲያዳከመኝ
ቀሚስሽን ይዤ
መትረፌ ገረመኝ።

## ገንዳው

እዚህ አሜሪካ በሀገረ ማርያም
በጊዜያዊ ቤቴ ጊዜያዊ በረንዳ
ቆሜ ሳነጣጥር
እየሁኝ መንገድ ዳር፥ ተገትሮ ያለ የቆሻሻ ገንዳ
ዳበው እንደ ጉድፍ
ወተቱም እንደ እድፍ
ልብሱም እንደ ቅጠል
በገንዳው ክርሰ ውስጥ፥ ይረግፋል እንደ ጠል፤

ያሜሪካ መልኳ
አይደለም ሕንጻዋ፥ ለማይ የሚነድለው
አይደለም መንገዷ፥ እንደቆለኛ ቅል የተወለወለው
አይደለም ፖሊስዋ፥ ዝሆን የሚያህለው
ያሜሪካ መልኳ፥ ጎልቶ የተሳለው
በገንዳዋ ላይ ነው፥ እመንገድ ዳር ባለው፤

ባገሬ ለማይ ሥር
ሰው ጠኔ ገፍትሮት፥ ሲወድቅ በመደዳ
ያሜሪካ ንስር
ላንዲት ለኒ ሆዱ፥ በጋን እያስቀዳ
እዚያ ማጣት እዳ
እዚህ ማትረፍ እዳ
እዚያ ባዶ ሞሰብ
እዚህ ሙሉ ገንዳ፤

ከዕለታት አንድ ቀን
በሰማያት እና በምድሪቱ ድንበር



ከእኛ ጎታ አጠገብ፥ የቆሻሻ ገንዳ ተቀምጦ ነበር
የለማይ አማልክት፥ አላጋጭ ቀልደኛ
"ራበን መግቡን"፥ ስንላቸው እኛ
ብዙ መና ጋግረው፥ ሲያዘንሙ ከለማይ
የእኛን ጎታ ስተው፥ ከተቱት ገንዳው ላይ፤

ከቶ ለምን ይሆን
ያፍሪቃ ሕፃናት፥ በደቦ ሚያለቅሱ
የወተቶች አዋሽ፥ የርጎ ሚሲሲፒ፥ በበዛበት ዓለም
ጤዛ የሚልሱ
የሹራብ ተራራ
የቡልኮ ጋራ
በበዛበት ዓለም፥ ጭጋግ የሚለብሱ
የምድር ጠቢባን
ለዚህ ግዙፍ ምስጢር፥ መልስ አገኘ ብላችሁ፥
ጠፈር አታስሱ
አሜሪካ ያለው፥ የቆሻሻ ገንዳ፥ ግጣሙ ሲከፈት
ወለል ይላል መልሱ።

## አንሶላየ ውስጥ ልሙት

ዘማች በሌት ገሰገሰ
ዘ ሟች ሆኖ ተመለሰ
ርቃን የኖረ ሜዳ፥ ያስከሬን ግምጃ ለበሰ፤

ለጀግናው ሐውልት ሥሩ፥ ጀብደኛውን ሸልሙት
እኔን ተዉኝ፥ አንሶላየ ውስጥ ልሙት

ፀሐይ በገባዖን ላይ
በጦርነት ሜዳ ሰማይ
ቁማ ትቅር፥ ከቶ አትጥለቅ
ጀግና ቢሻው ይተላለቅ
ተያይዞ ይጨማለቅ፤

የኔን ክብር ውሰዱና፥ ለጀብደኛው አሸከሙት
እኔን ተዉኝ፥ አንሶላየ ውስጥ ልሙት።

*(መነሻ - የይሁዳ አሚሽ "I want to die in my own bed")*



## ከተለየሁሽ ወድያ

ከተለየሁሽ ወድያ
ስንት ቅጥሮች ፈረሱ
ስንት ሕዝቦች ፈለሱ
ስንት ኮከቦች ተተኮሱ
ስንት ፀሐዮች ተለኮሱ
ስንት ዝነኞች ተረሱ
ስንቶች ካመድ ተነሱ፤

ስንት ባሕሮች ደረቁ
ስንት አለቶች ውሀ አፈለቁ
ስንቶች አማልከት ሞቁ
ስንት ደናግል ገለሞቱ፤

ባለት አጥር የከለሉት
የማይጣስ ጥሶ ሾልኮ
በብረት ጣት የጨበጡት
ከመዳፍ ሥር አፈትልኮ
ምንም ነጻ መስሎ ቢታይ
ሁሉም የጊዜ ግዳይ
ሁሉም የጊዜ ምርኮ፤

አንቺ ከየት አመጣሽው
የለውጥን ሞገድ መግቻ
ባስቀመጥሁሽ ያገኘሁሽ
አንቺን ብቻ፤ አንቺን ብቻ።

## ተስፋ እንደ ምትሐት

ነጋ

የግዜር ስውር መዳፍ
ልክ እንደፓፒረስ፥ እንደግብጦች መጣፍ
ወይም እንደጥንቱ፥ ያባጅፋር ምንጣፍ
ጨለማውን ሰቦ፥ በወግ ሸበለለ
ሰማይ የጠፈር ዓይን፥ ብርሃን ተኳለ
ከዶሮ ጩኸት ውስጥ፥ አዲስ ጎሕ ተወልዶ
ፍጥረቱ በሙሉ፥ ማርያም ማርያሜ አለ፤

ነጋ

አልጋየን ሰብሬ
አንሶላ ተርትሬ
ባዲሱ ጉልበቴ
በታደለ አሞቴ
ልኖር ተዘጋጀሁ
እንደጣዝማ ቅንጣት
ከሚጣፍጥ ሞቴ
ትንሳኤየን ዋጀሁ፤

ነጋ

እንደምትሐተኛ፥ ተስፋ ሲያታልለኝ
አዲሱ ማለዳ፥ "ዛሬን ሞክር" ሲለኝ
የዛሬው እጣየ
ከትናንት ጣጣየ
የሚለይ መስለኝ።



## በቃኝ

እሳት ሆኘ ስነድ፥ አንቺ ቆፈን ወርሶሽ
ሎሚ ብወረውር፥ እንቧይ ሆኖ ደርሶሽ
ዝምድና ሳያንሰን፥ እየቆየሽ ባዳ
መላመድ ሳይጎድለን፥ እያደርሽ እንግዳ፤

እንግዲህ ደህና ሁኚ!

ምኞቴም በረደ፥ ቁጣየም አለፈ
ከእድሉ ጋር ታግሎ፥ ማነው ያሸነፈ።

## በሞቷ ፊትለፊት

በቀደም ደወለች፤
አወጋች አወጋሁ
በለተመጨረሻ
ደና ሰንብች ብየ፥ የስልኬን አፍ ዘጋሁ፤

ከዚያም ቀናት አልፈው
ወራት እንደቅጠል፥ እግሬ ሥር ረግፈው
ልጅ ሆና የማውቃት፥ እናቷን አክለች
ዘጠኝ ወር አርግዛ፥ ሞት ተገላገለችኝ፤

ምን አሸዋ ቢያልቡ
ነፋስ ቢጋልቡ
ደመናውን ጠርበው፥ ሐውልት ቢያስገነቡ
ሞትና ክስመት ነው፥ የተፈጥሮ ግቡ
ብየ እንዳልጽናና
በሞቷ ፊትለፊት፥ ሀሳብ ሁሉ መና
ምክር ሁሉ እና
እንባን አይገድብም፥ የሰው ፍልስፍና፤

በፍራሻችን ሥር፥ ቃሬዛ ተጣብቆ
በልብሳችን ገበር፥ ከፈን ተደብቆ
የአድሩ ጥሩንባ፥ ከሙዚቃው ልቆ
በዘንድሮ ጣቶች፥ ክርሞ ላይነካ
ደና ሰንብች ማለት፥ ዘበት ኑሯል ለካ።

*(ይህ ግጥም፥ ለእህቴ ለከብርት ሥዩም፣ እንዲሁም እሷን ለመሰሉ፣ ለመውለድ በአምቡላንስ ወደ ሆስፒታል ገብተው በቃሬዛ ለሚወጡ ያገሬ እናቶች መታወሻ ይሁንልኝ።)*



## የመኖር ትርጉሙ

የመኖር ትርጉሙ
የንባ ቅብብል ነው፥ በትውልዶች ማህል
አባትህ ያነባው፥ ላንተም ይደርስሃል፤
ሰው የሆንሁ ለታ፥ ደርሶኛል ይህ እጣ
አልቅሼ እንደገባሁ
አስለቅሼ ልውጣ።

## አስታራቂ የለም

ጠብ ምድርን ባይሞላት
አቤል ባይፈጠር
አቤል ያቤል ጠላት
አቤል የራሱ ጠር
አንድ ሰው ከሁለት፥ ተከፍሎ ሲፋለም
ሸምጋይ
ወይ ገላጋይ
አስታራቂ የለም።



## ላንድ መስቲካ ሻጭ ብላቴና

በደብተርሽ ምትክ፥ ትንሽ ሱቅ ታቅፈሽ
ካልፎ ሂያጅ አግር ሥር፥ እንደ ድንቢጥ ከንፈሽ
ጋሼ ግዙኝ ስትይ፥ አንጋጠሽ ወደ ላይ
ለጉድ ተጎልቶ፥ ምታደርጊውን ሳይ
ራሴስ ይታመም፥ ምላሴን ምን ነካው
ግራዋ ይመስል፥ መረረኝ መስቲካው፤

አፈር ጠጠር ለብሶ፥ በዶዘር ተድጦ
መስኩ ከነገርፉ
ሰማይ ከነዶፉ
ለጌቶች ተሸጦ
አተር ነው እያሉ፥ አፈር ዘግኖ መፍጨት
ገነት ነው እያሉ፥ መስከ ላይ መፈንጨት
ጠበል ነው እያሉ፥ ተጎርፉ መራጨት
ይህንን ማን ሰጥቶሽ
ገና በልጅነት፥ ልጅነት አምልጦሽ፤

በምቢልታ በዋሽንት፥ በከበሮ ታጥሮ
በከራር ተማግሮ
በቆመ ከተማ
እምባሽ ቅኝት የለው፥ ለሰው አይሰማ፤

ጠዋት የፎከረ፥ ቀትር ላይ ሲረታ
ዛሬ ዝሎ ሲወድቅ፥ ትናንት የበረታ
ኑሮን ያህል ሸክም፥ ያላንቀልባ ሲያዝል
ምን ጸጋ ለብሶ ነው፥ ትከሻሽ የማይዝል።

## ግን አንድ ሰው አለ

እርጅና ሲጫንሽ
እድሜ ተጠራቅሞ፥ እንዳስም ሲያፍንሽ
ሽበት እንዳመዳይ
በጭንቅላትሽ ላይ
በድንገት ሲፈላ
ያይንሽ ከረጢቱ፥ በንቅልፍሽ ሲሞላ
ምድጃ ዳር ሆነሽ
መጣፍሽን ከፍተሽ
ያለፈውን ዘመን፥ ገልጠሽ ስታነቢ
የኔን ቃል አስቢ፤

ሰንቶች አፈቀሩት፥ በሐቅ በይስሙላ
የገጽሽን አበል፥ የውበትሽን አፍላ
ግን አንድ ሰው አለ
ከሌሎች ወንዶች ጋር፥ ያልተመሳሰለ
በዕጹብ ድንቋ ነፍስሽ፥ ፍቅር የነደደ
የመልከሽ ጸደይ ሲያልፍ
ልክ እንደ መስቀል ወፍ፥ ጥሎሽ ያልነጎደ።

*(መነሻ - የዊሊያም የትስ "When you are old")*



## በምናልባት ኑሮ

አይቦዝን እንቀልባው
አይሞላም ጉድጓዱ
ሺሆች ሞተው ሲያድሩ
ሺሆች ተወለዱ
ይመሻል ይነጋል
ያው እንደልማዱ፤

መሬት ባሕር ሆኖ፥ ድህን ሰለቀጠው
ትልልቁ ቪላ፥ ትንሹን ቤት ዋጠው
በመስታወት ጫካ፥ በጡብ በብረት ደን
አየሁ ባደባባይ፥ ሰው በሰው ሲታደን፤

ማን በገላገለኝ፥ የጄን ሰዓት ሰብሮ
በምናልባት አገር፥ በምናልባት ኑሮ
የመጣው ይምጣ እንጂ፥ ማን ያቅዳል ደፍሮ።

## ያንድ ምሽት ናፍቆት

ዛሬ ታምራለች ጨረቃ
ፊትሽን ፊቷ ላይ፥ እንደጭንብል አጥልቃ
እንሆ እኔም ቁምያለሁ
የዛፉን መልክ መልኬ አድርጌ
በሩቅ ማየት ተፈቅዶልኝ
መንካቱን ግን ተነፍጌ።



## የምድረበዳ በረከት

አንዲት ብርጭቆ ወይን፥
        አንዲት ጤፍ እንጀራ፥ አንዲት አሪፍ ቅኔ
እነዚህ ባሉበት፥ በምድረበዳ ላይ፥ ቁጭ ካልሽ ከጎኔ
ሌላው ምን ይሠራል
ምድረበዳው ሁሉ፥ ዓደይ ለብሶ ያድራል።

*(መነሻ - የኦማር ካያም "Rubaiyat")*

## ላጣሽ አቅም አጣሁ

ዓለማዊ ልቤ፥ ለበሰልሽ ዳባ፥ ምናኔ ተመኘ
በናቴ ቀብር ላይ፥ የጠፋብኝ እንባ፥ ፊቴ ላይ ተገኘ
ላጣሽ አቅም አጣሁ፤

የሳምሶንን ገድል
ያላዛርን እድል
ያቡየን ተአምር
ተቀብየ ነበር፥ ቄስ እንዳስተማረኝ
አንቺን አጣሁ ብየ፥ ማመኑ ቸገረኝ፤

ከረምቱ ጨከነ
ጨላለመ ጋራው
በረዶና ጭፍራው
ከዋሻቸው ወጡ
ዛፎች ተመለጡ
ከምልአት ጎደሉ
ላባቸውን ያጡ
አሞሮች መሰሉ፤

ልረሳሽ አልቻልኩም፥ ልረሳሽ እልና
ፊትሽን አትመሽ፥ በየብስ በደመና
ከንፈርሽ ያውና
ፈገግታሽ ያውና
ውብ ዓይንሽ ያውና።



## ጠብ እና ጥበብ

"ተዋጋ ብሎ ቢሰጠው ጋሻ
ለናቱ ሰጣት፥ የእበት ማፈሻ"
(አገርኛ ቀረርቶ)

የጥበብ ሁሉ መጀመሪያ
ጠብን መፍራት
ጦርን መግራት
ከጋሻ፥ የእበት ማፈሻ መሥራት።

## አለሽ ወይ

አለሽ ወይ አለሽ ወይ
አለሽ ወይ በጤና
ይመስገን ደመና፤

በገበሬው እጥንት፥ መሬቴን እያረስሁ
እንጀራ ሲጠፋ፥ ገበሬ እየኀረስሁ
አለሁኝ በደህና
ይመስገን ደመና፤

ሰው ሲያፈርስ እያየሁ፥ ሰው ሆኖ ቡልዶዘር
አንዱ ጭቃ ነገድ፥ ሌላው የብረት ዘር
በፈረሰ ሰው ላይ፥ በቆመ ሰገነት
ሲአል እናቱ ላይ፥ በታነጸ ገነት
ይህን ኑሮ ብለው፥ ጥቂቶች ሲኖሩ
ያለምንም ጸጸት፥ ያለምንም ሀፍረት
ይህንን እያየሁ፥ በታላቅ ጽሞና
አለሁኝ በደህና
ይመስገን ደመና፤

በምኞት መዲና፥ የምንዱባን ትዝብት፥
እንደሐሩር ልፎኝ
በጠዳው ጎዳና
ለማኝ ብላቴና
እንደጉቶ አናቅፎኝ
ልክ እንደገባሮች፥ ለመኖር እያቀድሁ
በጌቶች ሞሰብም፥ እጄን እየሰደድሁ
አለሁኝ በደህና
ይመስገን ደመና፤



ወይ በሩን አሳይን፥ ወይ ጠቁሚን መላ
ማዕበል ሲቃረብ፥ ያመልጣል ሺመላ
በነፋሰ ገጽ ፊት፥ ይሸሻል ደመና
የኔ እዚም ያለበት፥ ያገሬ ሰው ግና
በሥጋ ደም እጥንት፥ የተሠራ አይመስል
እንደኮንሶ ሐውልት፥ የመቃብር ምስል
አይሸሽ አያባርር፥ ወይ አይተነፍሰ ቃል
አንጨት ሆኖ ቆሞ፥ ለደድ ይጠብቃል፤

ይህንን እያየሁ
ሁኜ በጥሞና
አለሁኝ በደህና
ይመስገን ደመና፤

አንች ግን አለሽ ወይ፥ እኔ አለሁ በደህና
አለሁ ግርምት ወሮኝ
ምላሱን በምላጭ እንደተሰለበ
ምናገረው ኖሮኝ
የምለው ቸግሮኝ።

## በረከተ መርገም ፪

ነጭና ጥቁር ነው፥ የኔ አመዳም ዓለም
ቴሌቪዥኔ ግን፥ ባለ ህብረቀለም
ምንም እንኳ ቲቪው፥ ሳሎኔ ውስጥ ቢኖር
የቲቪው ኑሮ ግን፥ ሳሎኔ ውስጥ የለም፤

የቆንጆ ሰራዊት፥ የሕንጻ ሰንሰለት
የማያልቅ አዱኛ፥ የማይነጥፍ ውበት
ያልፋል በሰከሪኔ
ይህንን እያየሁ፥ ቀርከሀ ሰፋ ላይ፣ ተኝቻለሁ እኔ
እድሜ ለቲቪዬ፥ ለጉምዥት ማሽኔ
የቲቪ ፈብራኪ፥ የልቦናህ ፍሬ ፍትሕ  የጎደለው
ኢትዮጵያዊው ገብርኤል፥ ቁልቢ ላይ ያለው
በነበልባል ሰይፉ፥ በሚንቀለቀለው
እንድጊዜ ሰንዝሮ፥ ጎንህን ይንቀለው!

ኮምፒውተር የሚሏት፥ የደብተራ ሳጥን፥
ከመጣች ጀምሮ
በወግ መኖር ቀረ፥ እስማት ሆነ ኑሮ
ከተፈጥሮ ሸሸ፥ ሰው ከሰው መነነ
መኖርና መሞት፥ ክሊክ ማድረግ ሆነ፤

ወንበር ላይ ተጥዶ፥ ወንበር ላይ እንዲያረጅ
ትውልዴ ላይ እዚም፥ የጣልከበት ፈረንጅ
የፌስቡክ ፈብራኪ፥ ጎረምሳ ዲታ ሰው
የግፍ ንብረትህን፥ በልተህ ሳትጨርሰው
የየካው ሚካኤል፥ ዓይንህን ያፍሰው!



የሹክሹክታ ዘመን፥ ትናንትና አለፈ
እንደደጋ መስኖ፥ ምላስ ተጠለፈ
እቤት ተቀምጬ፥ ባለሰልጣን ሳማ
ቤቱ ተቀምጦ፥ እጅሬ እንዲሰማ
በእጅ የማይዳሰስ፥ የሐሜት ሰንሰለት
የዘረጋህለት
የሞባይል ፈጣሪ፥ የቴሌፎን ጌታ
በኖርክበት ዘመን፥ ባለህበት ቦታ
አቡነ አረጋዊ፥ ይጣሉህ በቴስታ!

*(መነሻ - የኃይሉ ገብረዮሐንስ "በረከተ መርገም")*

## ኢትዮጵያዊ ነኝ

ኑሮ ቢገፋኝ፥ የማልወድቅለት
እንዳከሱም ድንጋይ፥ እንደ ሮሐ እለት
የጊዜ ሞገድ፥ ያላደቀቀኝ
የመከራ ዶፍ፥ ያልነቀነቀኝ
ለሙሾ ሲያጬኝ፥ ቅኔ የምቀኝ
በግራ ሲሉኝ፥ የምገኝ በቀኝ
ኢትዮጵያዊ ነኝ፤

ከዋርካ ባጥር፥ ከምቧይ ተልቄ
ከፀሐይ ባንሰም፥ ከኩራዝ ልቄ
ተምድረ በዳ፥ ጅረት አፍልቄ
ጥሜን የምቆርጥ፥ በፍኝ ጠልቄ
ኢትዮጵያዊ ነኝ፤

ግትር ጠላቴን፥ ባጭር እንካሴ
ራስ ምታቴን፥ በዳማከሴ
ነቅየ ምጥል
ነገር በነገር፥ የማብጠለጥል
ለወዳጆቼ፥ ዓደይ ምነቅል
በጠላቴ ፊት፥ ቀንድ የማበቅል
ልክ እንደዋልያ፥ ተራራ መራጭ
ልክ እንዳሞራ፥ ብርንዶ ቆራጭ
ኢትዮጵያዊ ነኝ፤

እንደመሀረብ፥ ቤቴን በኪሴ
እንደንቅሳት፥ ተሰፋን በጥርሴ
ይዤ የምዞር
ከቦታ ቦታ
በዘብ በኬላ፥ የማልገታ
ኢትዮጵያዊ ነኝ።



## ሱ !!

እንደሰንበሌጥ ቤት፥ ምድራቱን እፍርሶ
ማድጋ ይመስል፥ ጀምበርን ከሰከሶ
እስኪያስናብተን፥ ጉዳችን ሳይፈላ
እንፍጠን ለተድላ
ልብ ያለህ፥ ልብስ በል
ሆድ ያለህ፥ ሆድ ሙላ፤

የወይራው የጥዱ፥ ችግኙ ይነቀል
በመስኩ በሸጡ፥ ጭገር ብቻ ይብቀል
መቀነትሽን ፍቺ፥ ሸምቀቆህን ፍታ
ግባባት ጠብድለህ፥ ታስገባህ ተከፍታ
አጥምቃት ተጠመቅ
ዓይንህን ጨፍነህ
ዕውር እድል እምነህ
ግባ ተመቀመቅ!

ብትን ከስከሰ ሰትል
ሕይወት ከ'ጅ እምልጣ፥ ልክ እንደ ብርሌ
እጣቸው አንድ ነው፥ ድንግልና ሸሌ
ዋጋቸው መሳ ነው፥ ጭምትና እለሌ፤

ሰብከት ደና ሰንብት፥ ወግድ አትሮኖሱ
ጭላንጭል የለውም፥ ቀፎ ነው ፋኖሱ
መስጠማችን ላይቀር፥ በየውቅያኖሱ
ተነሱ ደንሱ!

ሱ !!

## እንጉርጉሮየ

ትናንትና ማታ
ላሟሟሽ ሲገባኝ፥ እንዳሞሌ አጥቤሽ
በመጨረስ ፋንታ
ሰነገ ቆጥቤሽ፥ አስተርፌሽ ሰሰው
የፀፀት ሱናሚ፥ ዓሰሜን እመሰው፤

ምነው ቢቻል ኖሮ
ፈገግታሽን ጳጥሮ
ሙዳይ ውስጥ መደበቅ
ጃንደረባ ቀጥሮ
ጭንሽን ማስጠበቅ
ከፍት ልቤን ይዤ፥ ዝግ ደጅሽን ጠናሁ
በሰበብ ወድጄሽ፥ ያሰ ሰበብ ቀናሁ፤

ፍቅር በተባሰ፥ ግራ ገቢ ነገር
ከጨመተው አገር
ከሰከነው ቀየ
መናፍቅ ይመስል፥ ባዋጅ ተነጥየ
እንደካፖርቴ ቁልፍ፥ ልቤን የትም ጥየ፤

የትም ስከተልሽ
የትም ሆኖ እድልሽ
ሁሉ ያንች ወዳጅ
ሁሉ ባላንጣየ
መፈቀር ሆኖ ጣሽ፥ መቅናት ሆኖ ጣየ
ላንቺ ብስል ፍሬ፥ ለኔ ገለባ ግርድ
ላንቺ እቅፍ አበባ፥ ለኔ እቅፍ ሙሉ ብርድ
ማነው የበየነው፥ ይህን ግፈኛ ፍርድ።



## አስቢኝ

ጭር ባለው ሌሊት ማሀል
ከመስኮትሽ ባሻገር፥ ባለው አውራ ጎዳና
ኩልል እንዳሰ ምንጭ፥ የሚፈልቅ ብቸኛ ዳና
ስትሰሚ፤

አስቢኝ

ጨረቃ፥ የወፍ ቤት መስላ
ሕዋ ዛፍ ላይ ተንጠልጥላ
በውበት ልብሽን ስትሞላ

እስቢኝ

ምንም እንኳ ሕይወትሽ
ቢሆንብሽ ያጋም እጥር
ከሾህ ጫካ ወድያ ማዶ
ያበባ እርሻ ባየሽ ቁጥር፤

አስቢኝ

የሚገፈትሩሽ ብረት ከንዶች፥ እዚም እዚያም ቢፈሉ
ጠላት ቢሆን ሣር ቅጠሉ
ከዱር ማሀል ተነጥሎ
እንደተመዘዘ እንግዳ ዛፍ
ተዘርግቶ ባየሽ ቁጥር
የሚያነሳሽ ልዝብ መዳፍ፤

እስቢኝ።

## ኬላ ነኝ

ስንቴ በሌሊት አስቀስሁ
በትራሴ ልብስ ላይ፥ የእንባ ፊደሌን ነቀስሁ
አምላክ ትቶኝ ቢተኛ፥ ጭንቁን ስጣራው ነግሬ
በለሰላሳ መዳፌ፥ ግድግዳየን ወግሬ
ስንቴ በሌሊት አስቀስሁ፤

ፍቅርን ተርቤ
ለመጭ ሂያጇው፥ የሥጋ ግብር አቅርቤ
ዙርያ ገባየ ኮርማ፥ አዳር ውሎየ ሰፈያ
የምሽቀጥ የምለወጥ፥ የጭን ገረድ የጭን ባርያ
ጭል ጭል የምል
እንደ አብሪ ትል
በሌሊት
ነፍስ እንዳለኝ የተካድሁኝ፥ ሥጋ ለባሽ አሻንጉሊት
ሊቅ ደቂቁ የሚቀዳው፥ ጭኔ የወረት ጠበል
አንዱን ጀርባ ሸኝቶ፥ አንዱን ደረት የምቀበል፤

ጓደኛ ኖሮኝ ባያቅም፥ ብዙ ጉደኞች አሉኝ
የሚያሳድሩኝ የማያውሉኝ
ደህና አመሸሽ እንጅ፥ ደህና ዋይ የማይሉኝ
የሚስታቸው ማሳረፍያ
የቡግራቸው ማራገፍያ
የጊዜያቸው ማሳለፍያ፤

ገና ሲያዩኝ፥ እንሶላ የሚያስቡ
ከግንባሬ ላይ፥ እምስ የሚያነቡ
ኬላ ነኝ የጠረፍ በር
መንገድ ላይ ያለሁ፥ እግዳሚ ወንበር
ያልፎ ሂያጅ መመላለሻ
የወጭ ወራጅ፥ ጊዜያዊ አድራሻ።



## ትዝታን ባጎበር

በንጹሕ ክፍል ውስጥ፥ በላባ ፍራሽ ላይ
እንኳን ሲተኙበት፥ ግልገል ሱሪ እውልቀው
ገና ሲያዩት ብቻ፥ በንቅልፍ የሚያጠምቀው
እዚያ ላይ ተኝቼ፥ ምቾቴን እጣለሁ
እንደ ጠላ ብቅል፥ እገላበጣለሁ፤

ባጭር ቁመትና፥ በጠባብ ደረት ውስጥ
ማደር እየጠላሁ
እንደ ሉባንጃ ጢስ፥ ክፍሉን እየሞላሁ
ብሰጠጥ ብሰፋ
ምቾት ዳናው ጠፋ
ረፍት ደብዛው ጠፋ፤

ይብላኝ እንጂ ለኔ
ይብላኝ ለክንዶቼ
ይብላኝ እንጂ ለኛ
ሌቱ ምን አለበት፥ ኮከብ አቅፎ ተኛ፤

ልረሳሽ ፈልጌ፥ ላወጣሽ ከደሜ
ፎቶሽን አውድሜ
ጽኑ ሐውልትሽን፥ ዶግ አመድ አድርጌ
ላወጣው ከደሜ፥ ደምሽን ጠርጌ
ልረሳሽ ፈልጌ፤

ፀረ-ቢምቢ እጎበር፥ ካልጋው በስተራስጌ
የተንጠለጠለው
ከቀሚስሽ ጋራ፥ ምን እመሳሰለው
ተዘግቶበት መስኮት፥ ተከርችሞበት በር
ተጠምዶ ጠበቀኝ፥ ትዝታሽ ባጎበር
ምቾቴን ያጣሁት፥ ለካ ለዚህ ነበር።

## እንደምነሽ ሸገር

እንደምነሽ ሸገር
እንደምነሽ ሸገር
የቤት አከራዩ፥ የጋሽ ጣሰው አገር
አንዱ የሚተከልሽ
ሌላው የሚነቅልሽ
የዘመቻ ድንኳን፤

ቡግርና ችግር፥ ካባቴ ወርሼ
ብኖርብሽ እንኳን
የማልቀየምሽ
ሁሌ የማልምሽ፤

Oh, my God ይመስገን
እኔ እንዳለሁ አለሁ፤

ከፊል ሩዝና፥ ከፊል ጤፍ እቡከቼ
እንጀራ ሚመስል፥ ሰጋጃ በልቼ
አዋጅና ዜና፥ ባይፎኔ ሰምቼ
ሐሜት ሲናፍቀኝ፥ በፓልቶክ አምቼ
ጥቃት ሲበዛብኝ፥ ፌስቡክ ላይ ሸፍቼ
በኮመንት ሩምታ፥ ጠላቴን ደፍቼ
እኔ እንዳለሁ አለሁ፤

እንደምነሽ ሸገር
እንደምነሽ ሸገር
የማይበገረው
ወር እየጠበቀ፥ የሚያንገራግረው
የቤት አከራዩ፥ የጋሽ ጣሰው አገር፤
የከሰመው ወንዝሽ
የነጠፈው ወዝሽ



የሚታየው ነጥፎ
እንደምነው ጣፎ
እንዴት ነው ቀበና
አሰቲ ድንጋይ ላጥምድ፥ መረብ ልጣልና፤

ልክ እንደነ ፓሪስ
እንደ ለንደን ሁላ
ፏፏቴም ባይኖርሽ፥ ሽቅብ የሚፈላ
ምንጭሽ ከማን ያንሳል
ከፈነዳ ቱቦ፥ የወጣ ሰገራ፥ ሰንጥቆሽ ይፈሳል፤

እንደምነሽ ሸገር
የቅጠላቅጠል፥ የፍራፍሬ አገር
አንድ ዘለላ ሙዝ፥ ልጠሽ ባታበይኝ
በሙዝ ልጣጭ ጠልፈሽ፥ ምታንከባልይኝ
አሳድገሽኛል፥ በማርና ወተት
የተሞላ ተረት
እየተረከሽልኝ
ጥማቴን በጥማት እያረካሽልኝ፤

እንደምነሽ ሸገር
Oh my God ይመስገን
እኔ እንዳለሁ አለሁ፤

ሰርቼ ቀፍየ
ሲነጋም ከፍየ
ሲመሽም ከፍየ
ሥጋ ምታወፍር፥ ነፍስ የምታሳሳ
ዘናጭ አልጋ ሰጥታ፥ እንቅልፍ በምትነሳ
አገር ላይ ተጥየ።

## ወይ ገራምነቴ

ወይ ገራምነቴ፥ ወይ አለማወቄ
አውቶብሴን ትቼ፥ መሲሕ መጠበቄ
በመስጊዳም አገር
በገዳማም አገር
የከንፍ ድምፅ ይሰማል፥ ተርገብጋቢ ነገር
የመላክ አይደለም
ከመአት የሚያድን
ያሞራ ነው እንጅ፥ የሚበላ በድን።



## አገሬ

አገርን ለፈሪ፥ አይሰጡም አደራ
ዳር አድርጎት ያድራል፥ የማህሉን ስፍራ፤

አገርን ለፈሪ፥ አደራ ብሰጠው
የዘላለም ቤቴን፥ ባንድ አዳር ለወጠው፤

አባ ነጋ ሞቶ
አባ ጽልመት መጥቶ
አገሬ እንደ ዛጎል፥ እያብረቀረቀች
ከባሕር ተገፍታ፥ የብስ ላይ ወደቀች።

## መኖር ወይስ አለመኖር

የኑሮን ትርጉም የምትሹ
መኖር ወይስ አለመኖር
ይህ ነው እንቆቅልሹ
መድከም
የኑሮን ቀንበር መሸከም
ወይስ
ሕይወት ሚሉትን ደዌ፥ በሞት ወጌሻ ማከም?

የርጅናን ንቀት ልግጫ
የጌቶችን ርግጫ
የከሸፈ ፍቅርን ጡጫ
የጉልቤውን እብሪት ናዳ
በቀልደኛ ዳኞች ችሎት
ውሀ መልስ፥ ውሀ ቅዳ
ይህን ሁሉ የኑሮ እዳ
ችሎ
አሜን ብሎ
መቀጠል
ወይስ ራስን በራስ፥ ማንጠልጠል
መሞት ማንቀላፋቱ
ማራገፍ ሥጋን ከነከፋቱ
ቢቻልማ መልካም ነበር፤

ግና በሰው
ያልታሰሰው
የመቃብር ስውር አገር
የሄዱትን ውጦ ሚያስቀር፥ ዜናው እንዳይነገር
ግርማው ወኔን ያሳጣል
ከማታውቀው ወለላ ሞት፥ ሬት ኑሮን ያስመርጣል።

*(ከሼክስፒር "Hamlet" ተውኔት የተመለሰ)*



## ታሪክ የሆነ ሌሊት

እንደቡዳ መዳኒት
ጡትሽ ማሀል ተጠምጀ
ሰማይ ቀሊል መሆኑን ከጀ
የብሱ ጠጣር መሆኑን ከጀ
በግሬ ሽቅብ በርሬ፥ በከንፎቸ ተራምጀ፤

አይታጠፉት ታጥፈሽ
ገላሽን እንደ ጽዋ ገልብጠሽ
ገላየን እንደ ሽቦ ቆልምመሼ
አይጣመሙት ተጣምሜ
ከፍ ብየ ባትሽን፥ ዝቅ ብየ እንገትሽን ሰሜ
እንደገረድ ንብ፥ በገዛ ማሬ ሰጥሜ፤

ስትነከሽኝ ሕመሜን አዳፍኜ
እሪታየን አፍኘ
ከላይ ውሀ ውሀ እያልሁኝ፥ ከታች ምንጭሽን ደፍኜ
አይደረግን ስንዳረግ፤ አይሆኑት ሆነሽ፥ ሆኜ
ደስታ
እንደባርያ በሽታ
ሳይጥሰን
ተድላ ጨርሶ ሳይገድለን
ሌቱ ከላያችን ላይ፥ ዳሱን ንዶ ገላገለን፤

ያው እንግዲህ ኀሕ ቀደደ፥ ታሪክ ሆነ የሌት ጣሙ
አለሎ እንደሚገፋ ጉንዳን፥ ሊባዝን ነው ዓለሙ
የማለዳ ሰማይ ቢያምር፥ ቢማርከም በቀለሙ
ሲያዩት ድባብ ቢመስልም፥ የቀንበር ያክል
ነው ሸክሙ።

## ወዴት

ዞትር የሚስቁት፥ ወዴት ገቡ አበቦች
የሚፍለቀለቁት፥ የታሉ ኮከቦች
ምን አጋይቶት ይሆን፥ ሰማይ የከለለ
ምን ነካው ደመናው፥ ኩበት የመሰለ
አስፋልቱስ የት ሄደ፥ የተለጠለጠው
ወንዙስ ተሰደደ፥ ድልድዩስ ምን ዋጠው
የት ተነነ ጫካው
የት መነነ ዋርካው
በለምለም ጣቶቹ፥ ሰማይ የሚነካው
ዳበስኩኝ
ፈተሸኩኝ
መረመርሁኝ ካርታ
አገሬን አጣኋት፥ ባለቀመጥኋት ቦታ።



## ይድረስ ለጥም ሚኒስትር

ይድረስ ለጥም ሚኒስትር
ላልጠጣነው ለሚያስከፍሉ
ጥም በቧንቧ ለሚያከፋፍሉ
እንዴት አሉ
እንዴት ዋሉ፤

አለሁ በከፍተኛ ጥም
ባገሬ ተሰፋ ብቆርጥም
በጅቡቲ እየተጽናናሁ
አቧራየን እየጠጣሁ
ጠጠሮቼን እየሸናሁ፤

ዘለቅሁት ይህን አመት
የተሸመነ አድፍ ለብሼ
እንደ ማለዳ ድመት፥ ፊቴን በምራቁ አብሼ
ሺህ ጀሪካን ከፊቴ
ሺህ ጀሪካን ከኋላየ፥ አግተልትየ አሰልፌ
ምድረ በዳውን በመስኖ፥ ቤቴ ድረስ ጠልፌ።

## እንባየን የት ላርገው

ቀና በል ይሉኛል፥ ወዴት ልበል ቀና
ከላይ ተደፍቶብኝ፥ አገር እንደቁና
ጣራው ባጡ ቀርቦኝ
በር አልባ ግድግዳ፥ እንደ ዝናር ከቦኝ
በጫጩት ጉልበቴ፥ እየተወራጨሁ
እንባየን ዘግኘ፥ ሽቅብ እየረጨሁ
ወደ አማልክት ብጮህ፥ ጸሎቴን አይሰሙት
በየት በኩል ኖሬ፥ በየት በኩል ልሙት፤

በምን ይገለጻል፥ የትውልዴ አበሳ
ከመንበርክከ ብዛት፥ መራመድ የረሳ
ያልፋል ተለጉሞ
ያልፋል ተከርችሞ
የጉልበቱን ኮቴ፥ ምድር ላይ አትሞ፤

ወፈፌ ቀን አልፎ፥ አብድ ቀን ሲመጣ
ማልቀስ አመጽ ሲሆን፥ በሽንጎ ሚያስቀጣ
እንባየን የት ላርገው
ወዴት ልሸሽገው?



## አገር እንቁጣጣሽ

አገር እንቁጣጣሽ
የ'ዳ ከንድሽ አቅፎኝ
ያሳር ከንፍሽ አቅፎኝ
ዕንቁሽን ስመኘው፥ ጣጣሽ ብቻ ተርፎኝ
መኖርን ስፈራ፥ መሞትም ስፈራ
ካየር ንብረት በቀር፥ ንብረት ሳላፈራ
ወሩ ተጠራቅሞ፥ አንድ ደርዘን ሞልቶ
እንደባለጌ ልጅ፥ በሩን በግሩ ከፍቶ
አዲስ ዘመን ገባ፤

አዲስ አመት ገባ
ያለ መስቀል ወፎች፥ ያለ ዓደይ አበባ
በግዜርሠራሽ ማማ
ቁራ ብቻ ሰፍሯል
የመስቀል ወፍማ
ወይ አገር ለውጧል
ወይ ልብሱን ቀይሯል፤

አዲስ አመት ገባ
በቁጤማ ምትክ፥ ብሎኬት ጎዝጉዞ
በቅፍ ዓደይ ምትክ፥ ጉንጉን ሽቦ ይዞ
በሉባንጃ ምትክ፥ አቧራ እያጤሰ
በፈንድሻ ምትክ፥ ጠጠር እያፈሰ፤

አዲስ አመት ገባ
አዲስ እንዲህ ዋዛ
ተፈጥሮ በውበት፥ መንፈሴን ሳይገዛ
በመአዛው ሳይዋጅ
መስከረም መግባቱን በሬድዮ ልስማው?
እንደ መንግሥት አዋጅ።

## ምኞት እሽሩሩ

የምኞቴን ስእል፥ ከግንባሬ አንስቼ
ብብቴ ሥር ደበቅሁ
በሰውር ጎምዥቼሽ፥ ስንት ዘመን ማቀቅሁ
ሳትቀጥሪኝ ቁጭ ብየ፥ አንቺን እየጠበቅሁ።



## እባ ይፍቱኝ

አባ ይፍቱኝ
ሲአል አለ ሲሉኝ፥ የለም ብየ ከጀ
የባልቴት ተረት ነው፥ በማለት ቀልጀ
እውቄ በድፍረት፥ በድያለሁና
ያንጹኝ በንስሐ፥ ያንሱኝ በቀኖና
ሲኦል ከነጭፍራው፥ በጉም ተሸፍኖ
እንዴት ሳላየው ኖርኩ፥ ካጠገቤ ሆኖ?

አባ ይፍቱኝ
ሰይጣን ብሎ ነገር፥ የተጭበረበረ
ዋዛ ነው ቧልት ነው፥ ብየ አስብ ነበረ
ይሄው እውነት ሆኖ፥ ዋዛና ተረቱ
ባይኔ በብረቱ
ዲያብሎስን አየሁት፥ በሸሚዝ ዘንጦ
እልፍ ግዳይ ጥሎ፥ ቸብቸቦ ጨብጦ

እባ
ልክ እንደ ብርሌ፥ እጥንት ሲከሰከሰ
እባይን እዋሽን፥ የሚያለንቅ ደም ሲፈስ
ለምለም ፍጥረት ሁላ፥ ወደ አመድ ሲመለስ
ልክ እንደ ጧፍ ሐውልት፥ ምስኪኖች ሲጋዩ
ምድጃው ዳር ሆነው፥ ይሄንን እያዩ
ገሃነም ከላይ ነው፥ ብለው መሳትዎ
እለዎ እንደፈቱኝ፥ እግዚሃር ይፍታዎ።

## ማንባት ነው ያሰኘኝ

ማንባት ነው ያሰኘኝ
ማልቀስ ነው ያማረኝ
ከቁጭቴ ጋራ፥ ወትሮ ከመታገል
የንባ ማድጋየን፥ ሰብሮ መገላገል
ማልቀስ ነው ያማረኝ፤

ያደራ ሳንዱቄ፥ ሲሰበር ከዳኑ
የባልንጀርነት፥ ሲጣስ ቃልኪዳኑ
መጋኛ ሲመታው
ዝምድና ሲከፋ
ፍቅር መሬት ከድታው
ባፍጢሙ ሲደፋ
የዳመነ ፊቴን፥ መዳፌ ውስጥ ልቅበር
የንባ ጋኔን ልሰበር፤

እኔ
እንደበሬ ያረስሁ
እህል የጎመጀሁ፥ ዝማምን የጎረስሁ
አዝመራ ያደረስሁ
ፍሬውን ያልቀመስሁ፤

እኔ
መከራን በበርሚል፥ መጥናናትን በፍኝ፥
ከዘመን ያተረፍሁ
እንቢይና ሙጃ፥ የወረሰው ሳሎን፥
ሳልፈልግ የታቀፍሁ
ቀስተ ደመናዬ፥ ምድጃ ሥር ወድቆ
እፍኝ አመድ ዝቆ፥ እፍኝ ትቢያ ቅሞ
ጥላሸቱን ጠግቦ፥ እድፍ ተሸክሞ
ኖህ ከነታሪኩ



ከነታይታኒኩ
አባሕር ውስጥ ሰጥሞ፥ ለማየት የበቃሁ
ፊቴን እየፈጀሁ፥ ደረት እየደቃሁ
ማልቀስ ነው ያማረኝ።

## ጥቂት ነው ምኞቴ

እኔ በሕይወቴ
ጥቂት ነው ምኞቴ
ከድፍና ከግፍ
የጠዳ
በረንዳ
እዛ ላይ መቆየት
ከሚደምን ዛፍ ላይ፥ ቅጠል ሲዘንብ ማየት፤

እኔ በሕይወቴ
ጤና ነው ምኞቴ
ለከርስ ጤፍ እንጀራ
ለነፍስ ባልንጀራ
ድከመቴን ሰናዘዝ ተግቶ ሚያዳምጠኝ
በደሌን መዝና ቀናና ማይሰጠኝ፤

እኔ በሕይወቴ
ጥቂት ነው ምኞቴ
ሊሞላ የቃጣው፥ ደርበብ ያለ ኑሮ
በስዊዝ ቤተ ነዋይ፥ ሶስት መቶ ሺ ዩሮ
ደሞ ከተቻለ፥ ቆንጆ ሚስት ወይዘሮ
እግዜርና ሰይጣን፥ ተጋግዘው የሳሏት
ቢቻል ትንሽ ቪላ፥ አስር ክፍሎች ያሏት፤

ግና ምኞቴ ሆይ
እንዲያው ለመሆኑ
ጥቂት ብሎ ነገር፤ ስንት ነው መጠኑ።



## ካንቺ ጋራ

ካንቺ ጋራ ሆኜ፤ የኖርኳቸው ጊዜያት
ያሳለፍኩት እድሜ
ጣፋጭ እንደጎጥያት
አጭር እንደጾጉሜ፤

አንቺ በላባ እግር፥ ደመና ላይ ቆመሽ
ሺ ሌሊት ከፊቴ፥ ሺ ሌት ከኋላየ
ኮከቡን በሞላ፥ በወረንጦ ለቅመሽ
ነዛሽው በላየ፤

ምንም እንኳ ሕዋው፥ ብርሃን ባያንሰው
ግርዶሽ ሆኖት ቆሟል፥ ይሄ ሰው ለዚያ ሰው
ግርዶሽ ቢነባበር፥ ኀይል የለው ባንቾ ፊት
መጋረጃው ሆነ፥ የብርሃን ወንፊት።

## ራሴን በራሴ

በውቄ ስዩም በዳዳ ደስታ ወየሳ
ዘብሔረ ማንኩሳ
ተጓዥ እንደሲራራ፥ በራሪ እንደሽመላ
ስደቱ የላሊበላ
እግሩ የፉየ ገላ፤

ቪላ ነቅሎ
ቤቱን ጥሎ
የሸማ ዳስ የሚቀልስ
ሲሻው ራሱን የሚያግዝ፥ ሲሻው ራሱን የሚመልስ
ሲወጣ የሳለውን ኮቴ፥ ሲገባ የሚደመሰስ
እሳት ከጭድ የሚያዛምድ
ቅል ከዱባ
የሚያጋባ፤

ተኩላ ከበግ የሚያላምድ
ባንዲት ብርጭቆ ጠላ፥ ባንዲት ስኒ ቡና ተድላ
ራሱን የሚያቀማጥል
በጮማ ቤት እንደመናኝ፥ የጎመን ፍሪዳ ሚጥል
አቀርቅሮ ደስታ ነዥ፥ ተኮሳትሮ ፈገግታ እዳይ
"So Proud to Live So Proud to Die ! "

በበረት የማይወሰን፥ በረኛ የማይመራ
የዱር በግ የዱር ፍየል፥ ባሻው የሚሰማራ
ከባብ ጋር የሚደንስ፥ በርግብ ጉባኤ የሚታደም
ነገሩ የጥንቅሽ ወዝ፥ ቃሉ የሸንኮራ ደም
ሞእ አንበሳ ዘብሔረ እዳ
አገሩን የማያምን፥ እገሩን የማይከዳ
ሜዳሊያው የሌት ኮከብ፥ ባንዲራው የጸደይ ሜዳ።



## ላንዲት ተመጽዋች ብላቴና

በቁሪስት ዓይን ውስጥ፥ ጠውልጋ እንዳትታይ
ከገጽታ ገንቢው፥ ግብዝ አደባባይ
የጠገበ ፖሊስ፥ የመንገድ አስከልካይ
ገፍቶ ያባረራት
ጥግ ይዛ የቆመች፥ እንደመንገድ መብራት
ትግሏ ጎደሎ ቀን፥ ግቧ የማታ ራት
ኩራቴን ላካፍላት፥ እፍረቷን ልጋራት፤

ድሪቶ ባይለብስ፥ ባካል ባይመነምን
ሁሉም ተመጽዋች ነው
እዱኛ ተሰጥቶት፥ ጤና የሚለምን
ጉልበት ስልጣን ተርፎት፥ ፍቅር የሚለምን
በጸጋ ተራቁቶ፥ ህልሙን የሚሸምን።

## ይድረስ

በገዛ ጆሮና በገዛ ዓይኖችሽ ላይ
ሙሉ ስልጣን ያለሽ
ከቶ እንደምን አለሽ፤

አለሁ እንደሸላው
እንደወፍ መነሻው
እንደወፍ መሸሻው
ፀሐይ እየሞቀ ከመተንፈስ በቀር፥ ሌላ እንደማይሻው፤

መኖር ብቻ ሲሆን፥ የሰው ልጅ እቅዱ
በሲኦል ቢኖርም፥ አይቀርም መልመዱ
እኔም ከመበላት፥ መብላት ይሻል ብዩ
ፍሪደም ቢርቀኝ፥ ፍሪዳየን ጥዩ
ነጻነት ቢርበኝ፥ እየበላሁ እህል
አለሁ ይህን ያህል
አለሁ ይህን ያህል።



## ስጦታሽን እንኪ

እመቤት ተፈጥሮ፥ ሰላም ሰላም ሰኪ
እዳሽን በቁና
ጸጋሽን በቆርኪ
ስትሰፍሪ መቀበል፥ ሰልችቶኛልና
ነጻነቱን እምጭ፥ ስጦታሽን እንኪ።

## ሰቆቃወ በውቄ

ሰፈሬ ሃያ ሁለት ማዞርያ ሆይ
የተመረጡቱ
ፎቅን በፎቅ ላይ ሲደርቱ
ጠጠር ዘርተው ወርቅ ሲያጭዱ
ያላረሱትን ሲያመርቱ፤

ሃያ ሁለት ማዞርያ ሆይ
አስር አመት አገልግየሽ
ያንገት ማግቢያ አንዴት አጣለሁ፤

ሃያ ሁለት ማዞርያ ሆይ
ብረሳሽ ቀኜ አስታውሳኝ
ማስታወሻየን አገልጣለሁ፤

ሃያ ሁለት ማዞርያ ሆይ
አያቴ ላንቺ አልሞተም?
በሰላም ቀን ሸሚዙን
በቀውጢው ቀን ምኒሽሩን ተኩሶ
በጦር ሜዳ ቅልጥሙን
በሰላም ቀን ብርሌውን ከስክሶ
ላንቺ ክብር አልመከተም?

ታዲያ አሁን ምነው መዳፍሽ ገፋኝ
የአንጀራ ልጅ ይመስል፣ ሲታዳይብኝ ከፋኝ፤

### *ስለ ጦቢያ የተነገረ ሽክም*

ኢትዮጵያ ቀይ ምንጣፏን ወደ አግዚአብሔር
ትዘረጋለች
ሰማዩን ሙጥኝ ስትል መሬቷን ትዘነጋለች



ቀስ በቀስ አዳኝዋ ገላምጧት ያልፋል
ገንዘብም ከክብር መንበሩ ባፍጢሙ ይደፋል
ጌቶችም የኢትዮጵያን የክብር ሉል ጨብጠው
ጥለው ረግጠው እንደብስል ቲማቲም አፍርጠው
አንሆ አዲሳባን ያማስኗታል
ሱዳንን ካንኮበር ጋር ያዋስኗታል
ምድሪቱን እንደጉልት አንጀራ
ወንዙንም እንደቢራ
ለሸማቹ ይሸጡታል፤

ያኔ ጌቶች
በርጫቸውን እንደጉማሬ ሲያደልቡ
ምመናን ሆይ ንስሐ ሳይሆን ጫካ ግቡ፤

በመጨረሻም ጌታ ይመጣል
መንኮራኩር ተሳፍሮ
አናም ጃንሜዳ ላይ ሰፍሮ
በጎችን በቀኝ ፍየሎችን በግራ አርጎ ይፈርዳል
በጎችን ላመት ባል
ፍየሎችን ላዘቦት ያርዳል።

## ሙግት

ጊዜ በሰው ሕይወት፥ ዘበት አይታከተው
እኔም ምላሽ ባጣም፥ መጠየቄን አልተው
ኩታ ገጠም ናቸው፥ እልፋና አሜጋ
እንዴት ቀን ይመሻል፥ በቅጡ ሳይነጋ?

ማን ዘረፈው ጠጉሬን?
ማን አሰረው እግሬን?
ጉልበቴን ምን በላው? እቅሜን ማን ወረሰው?
ተወልዶ ሳይጨርስ
እንዴት ያረጃል ሰው?



## ከዚህ ወድያ አልወድሽም

ከዚህ ወድያ እልወድሽም
የለም እወድሻለሁ ገና
ማፍቀር እጭር ቢሆንም
መርሳት ረጅም ነውና።

*(መነሻ - የፖል ኔሩዳ "Tonight I can write the saddest lines")*

## ማንም ግድ አይሰጠው

ቂጡን ዞፉን ላይ፥ ስለዘፈዘፈ
በጭቦ በኖረ፥ ድሀ እየዘረፈ
ንጉሥ የተባለ፥ የተቀባ ሌባ
ወትሮ ይወደሳል
ሚያመልከው አያጣም፥ ያውም በግዜር አምሳል፤

ግና ለገባሩ
ከላይ በትረ መንግሥት፥ ለሚቀጠቅጠው
ከታች የማጣት ፊት፥ ለሚገላምጠው
ማንም ግድ አይሰጠው፤

መቸም በዚች ዓለም፥ ታሪክ የሚያደላው
ቅልጥም ለሚሰብረው
አንገት ለሚቀላው
መንገድ ሲሰራለት፥ እግር ለሚቆርጠው
ሐውልት ሲሰራለት፥ ሐውልት ለሚያፈርሰው
ከማውደም በስተቀር፥ ተሰጥኦ ለሴለው
ስጦታ የለሽ ሰው፤

ሕይወት ለሚመልስ፥ ሕይወት ላመለጠው
ለወጌሻው ግና
ማንም ግድ አይሰጠው፤

ለሰላም ዝምታ፥ ላምባጓሮ መገን
ባዝማሪ ልሳን ላይ፥ ነፍስ ገዳይ ሲገን
ባቆላማጭ ምላስ፥ ፉኖ ሲመሰገን፤

ከሴት ማሕፀን እፍ
ከሀላዌ ደጃፍ
ጩቅላ



ተቀብላ
አትብት ለምትቆርጠው
ለዚያች አዋላጅ ሴት
ማንም ግድ አይሰጠው።

## ሙሾ ለከሰሙች ተፈጥሮ

ያኔ
ዛፎች ሳይረሸኑ
ማሮች ሳይመነጠሩ
መስኮች ሳይሸነሸኑ
በቆርቆሮ ሳይታጠሩ፤

ያኔ
ስንንና የዱር ዝሆን
የሎተሪ ስም ሳይሆን፤

ያኔ
ቤቶች በዝተው ተባዝተው
እንደከፉ አረም፥ መስኩን ሞልተው
ሐመልማሉን ቀጥቋጠውን፥ እንደባላጋራ ገፍተው
ግኡዝ ግሪሳ ሳይሆኑ፥ የምድርን አሸት ሚያበላሹ
በወንጭፍ የማይመቱ፥ በጠጠር የማይሸሹ፤

ያኔ
እዚም እዚያም ችፍግ ያለ፥ የበርና መስኮት ጭፍራ
የጭስ ጅረት የሚያመነጭ፥ የነተበ ድኩም ጣራ
በተፈጥሮ ውብ መልክ ላይ
እንደ ማድያት ሳይዘራ፤

ያኔ
ቢጋ ክረምት ሳይሉ፥ ወንዞች ሲገነፍሉ
ምንጮች በየመስኩ ላይ፥ እንደክረምት እግቢ ሲፈሉ፤

ያኔ
ገዴ ስትዘፍን፥ የጫካ ቆቅ ሲያስካካ
ያዋፍ ያራዊት ማህሌት፥ በመኪና እሪታ ሳይተካ



ከጥቁር አፈር ጋራ፥ እድሜያችንን እየፈጨን
ከደስታ እንባችን ጋር፥ ጅረት እየተራጨን
ልጅነታችንን ቀጨን፤

አሁን በድሜ ጎልምሰን
እጭተን፥ ጎጆ ቀልሰን
ቀድመውን ሳንቀላፉ፥ ወዳጆቻችን አልቅሰን፤

ለብሳናው ለግራሩ፥ ላለቀው በመጋዝ ታርዶ
ለተሰየፈው ዋርካ፥ ስደድ ለበላው ስርዶ
በቅጠሏ እየር ነዝታ፥ ጥኡም ፍሬዋን አብልታ
ላሳደገችን ሾላ፥ ለዚያች የዋህ የናት-ፋንታ
ምነው ሙሾ ማናወርድ
ምነው ደረት ማንመታ።

## ጉደኛ ስንኞች

፩

ከጥቂት አመታት በፊት የሆኑ ሸበቶ ሽማግሌ እኔንና አንድ አብሮአደጌን አፈላልገው አገኙንና ለጠቅላይ ሚኒስቲር መለስ የሚላክ አቤቱታ እንድንጽፍላቸው ማለዱን። የሆነ ጉልቤ በድሏቸዋል። (ምሬት አባርሮት ወደዚህ ገጽ የመጣውን አንባቢ ተጨማሪ ምሬት ላለማካፈል የሽማግሌውን በደል አልጽፈውም።)

ተገናኝተን ስንጨዋወት ስለግጥም ተነሳና አንድ ግጥም ቢቃሴ እንድወጣላቸው ጠየቁኝ። እሺ ብየ ሰባት መስመር ያህል እንዳነበብኩ "ምነው እንደ ረፋድ መንገድ አስረዘምኩብኝሳ?" ብለው እያፏጩ አቋረጡኝ።

"እንግዲህ የኔ ካልጣምዎት የርስዎን እንስማዋ" አልኩ ባኮረፈ ድምፅ።

"በጀ! ብትቀጥንም ጠጅ የሆነች ግጥም አለችኝ፤ አድምጥ እንግዲህ"

"ይቀጥሉ"

*"ዘመም ዘመም ብለን፤ እንደጤፍ ዘመመን*

*ዘመናችን አልቆ፤ አለን በሰው ዘመን።"*

"ዘመመን" የሚለውን ቃል ከዚያ በፊት ሰምቸው ስለማላውቅ ቤቴ ሂጄ መዝገበ ቃላቴን ጠየኩት። *(ዘመመን፤ ምላሳና ሽልጥ ጉቾ ድርድር። ደስታ ተክለወልድ፤ ዐዲስ የአማርኛ መዝገበ ቃላት፤* ገጽ 496።)

## ሙሾ እና ባለቅኔ

የጦዘ ደስታ የሚያነቃቃው ገጣሚ እንዳለ ሁሉ፣ ሥር የሰደደ ሐዘንም አሪፍ ስንኝ የሚወልድለት አለ። ከስሜቶች ሁሉ የሐዘንን ያክል በፍልስፍናና በኪነጥበብ ላይ ብርቱ አሻራውን ያሳረፈ የለም።

ሰው ንብረት ሊያካብት ይችላል። ድልና ስኬት በላይ በላዩ ሊቀዳጅ ይችላል። ቴክኖሎጂ የኑሮ ውጣውረዱን ሊያቀልለት ይችላል። እነዚህ ሁነቶች አልፎ ሂያጅ ደስታ ቢያቃምሱትም፥ ሐዘኑን ከምንጩ አያነጥፉለትም።

ትልቁ የሰው ልጅ የማይነጥፍ የሐዘን ምንጭ ሞት ነው። ሞት ከቀዳሚዎቻችን ጋር አቆራርጦናል፣ ገና ከወዳጆቻችን ጋራ ይለያየናል፤ ይህ ብቻ አይደለም። ከእለታት አንድ ቀን ከራሳችን ጋርም ይነጥለናል፤ እና ብናለቅስ ማን ይፈርድብናል?

ሞትን በደማቅ ፈገግታ እንድንቀበለው የሚጎተጉቱን ሰብከቶች ሲጎርፉ ኖረዋል፤ ግን ሰብከቶቹ ፍሬ ያላቸው አይመስሉም። እንዲያውም፥ ሞትን ለማቃለል የሚቀርብ ክርክር ብዙ ጊዜ ግብዝነት አያጣውም።

ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደሥላሴ "ጎህ ጽባሕ" በተባለ መጽሐፋቸው፤

> "ይህ አለም የተድላና የደስታ ብቻ ሳይሆን፥ የመከራና የሐዘንም ስለሆነ ብዙ ዘመን ቢኖሩ ጥቅሙ ምንድነው? ጥቂት ዘመን ቢኖሩስ ጉዳቱ ምንድነው?"

ብለው ሰብከዋል። ይቺን ከሰበኩ ከጥቂት አመታት በኋላ፥

ሙሾ አውራጆች ሞትን የከፉ ነገሮች ምንጭ አድርገው የሚያስቡትን ያህል በበጎ አይን የሚያዩበት ጊዜ ነበር። የመጀመርያ ቤት አከራዩ ቤት ግድግዳ ላይ ያየሁት በዳንቴል ላይ የተጣፈ የስንኝ ጥቅስ እስከዛሬ ድረስ አይረሳኝም፤

*"እግዜር ባንድ ነገር፤ አይጠረጠርም*
*የቸገረው ሞቶ፤ የደላው አይቀርም።"*

እግዜር ሀብት ጤና ውበትና ችሎታ ሲያከፋፍል ያዳላል፤ ግን በሞት ረገድ ሁሉን ያደላድላል። "ሞት እግዜር ሁሉንም እኩል የሚያደርግበት ብቸኛ ሥርአት ነው" የሚል ነው የገጣሚው ሀሳብ።

ሕይወት መራራ ፍሬዋን ብቻ በምትሰጥበት ማህበረሰብ ውስጥ ሞት የነጻነት ምንጭ ሆኖ ይቆጠራል።

ይህንንም ከዚህ የሙሾ ግጥም በላይ አሳምሮ የሚገልጠው ምን ሊኖር ይችላል?

*"ሞት ይቅር ይላሉ፤ ሞት ቢቀር አልወድም*
*አፈሩም ድንጋዩም፤ ከሰው ፊት አይከብድም"*

... ያው እንግዲህ ጎሕ ቀደደ፥ ታሪክ ሆነ የሌት ጣሙ

አለሎ እንደሚገፋ ጉንዳን፥ ሊባዝን ነው ዓለሙ

የማለዳ ሰማይ ቢያምር፥ ቢማርከም በቀለሙ

ሲያዩት ድባብ ቢመስልም፥ የቀንበር ያክል ነው ሸክሙ።



ዋጋ $10